# አማካኝተው በልዋት

ባሳለፍነው ሳምንት የቅንጅት አመራሮች ከእስር ቤት ይቅርታ ጠይቀው በመፈታታቸው በመዲናችን ነዋሪዎች የመነጋገሪያ ኣጀንዳ ሆኖ ሰንብተዋል:: ሰዎቹ የታሰሩበትንና ራሳቸውን ያመኑበት ወንጀል እጅግ ከባድና ተመጣጣኝ ቅጣት የተሰጠበት ቢሆንም የጠየቁት ይቅርታ መሰረት በማድረግ የህግ የበላይነት በማይፈታተን አኳኋን እስረኞቹ እንዲለቀቁ ፈቃደኛ በመሆን መንግስታችን እጅግ አኩሪ ስራ ሰርተዋል:: በዚህም የህግ የበላይነት ተረጋግጠዋል ብቻ ሳይሆን አገራችን ከፖለቲካ የበላይነት ወደ የህግ የበላይነት እንደተሸጋገረች በግልፅ የሚያሳይ ነው:: የታዳጊ ሃገሮች ፖለቲካ በምዕራባዊያን ፍላጎት በሚሽከረከርበት ዘመን የራሳችንን የፖለቲካ ጉዳይ ያለ ምንም የውጭ ጣልቃ ገብነት በራሳችን መፍታት መቻላችን ደግሞ ድሉ የበለጠ ያደርገዋል::

በይቅርታ ከእስር የተፈቱት ሰዎች ይቅርታውን ከልብ መቀበላቸው የማይጠራጠር ወገን እንዳለ ሁሉ ይቅርታ የጠየቁት ከእስር ለመውጣት እና የተቀረውን እድሜያቸው ከቤተሰቦቻቸው ለማሳፍ ስለ መረጡ ነው እንጂ ጥፋተኝነታቸው ከንፁህ ልቦና ተቀብለውት አይደለም የሚል ወገንም አለ:: ይህ ደግሞ ማረጋገጥ የሚቻው ሰዎቹ ራሳቸው ይቅርታ ለጠየቁት መንገስት እና ህዝብ በተግባር ሲያሳዩ ስራ ብቻ ነው::

ከእስር ከተፈቱ የቅንጅት አመራሮች አንዱ የሆኑት ኢንጂኔር ሃይሉ ሻወል ባለፈው ሳምንት ለ BBC ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደገለፁት ከሆነ ግን በርግጥም ይቅርታውን ከልብ መጠየቃቸውና መቀበላቸው የሚያጠራጥር ነው:: የይቅርታ ደብዳቤውን የፈረሙት በአስገዳጅ ሁኔታ ሆነው እንደሆነ ነበር የገለፁት:: ቀጠል አድርገውም እንደገለፁት ይቅርታውን የጠየቅኩት በእስር በደረሳቸው አስገዳጅ ሁኔታ ሳይሆን የፈረሙት አብሯቸው ከታሰሩት ጓደኞቻቸው መካከል ህፃናት ልጆች ያላቸውና ለህፃናቱ ሲሉ  እንደፈረሙ ገልፀዋል::

እሳቸው በፈጠሩት የፖለቲካ ምስቅልቅልና ተከሰውም ወንጀለኝነታቸውን በፍርድ ቤት ብይን ኣገኝቶ ራሳቸውም ይቅርታ በጠየቁበት ወንጀል ምክንያት የብዙ ወጣቶችና ህፃናት ህወት መጥፋቱ የማይዘነጋ ሲሆን ይቅርታ ጠይቀው ይቅርታው ተቀባይነት አግኝተው ከእስር ሲለቀቁ ሌላ ምክንያት በመፍጠር ይቅርታ የጠየቁት ለህፃናት ሲሉ እንደሆነ ሲናገሩ ስንሰማ ˜አማካኝተው በሏት˜ ከማለት ውጭ ሌላ ምንም ማለት አይቻልም::

የይቅርታ ደብዳበውን የፈረሙት ጥፋተኝነታቸው ከልብ አምነው እና ተቀብለው እንደሆነ ቢገልፁ የተቀረውን የፖለቲካ ሂወታቸውን እንዳይጎዱ ሲሉ በህፃናት ማሳበብ መምረጣቸው ግልፅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ይቅርታ የጠየቁት በድርጊታቸው ከልብ ተፀፅተው ሳይሆን ከእስር ለመውጣት ብቸኛ ቀዳዳ መሆኑ በመገመት ነው የሚለውን ጥርጣሬ ያጠናክረዋል፡፡

ኢንጂኔር ሃይሉ ሻወል በህፃናት የማመካኘት ስልታቸው አዲስ ነገር አይለም፡፡ ኢንጂኔር ሃይሉ ከእስር የመፈታታቸው ምክንያት ህፃናት መሆናቸውን ለBBC ሲገልፁ ትዝ ያለኝ በ1997 ዓ.ም. ከ BBC ሃርድ ቶክ ጋዜጠኛ ስቴፈን ሰኩር ያደደረጉት ቃለ ምልልስ ነበር፡፡ በዛን ጊዜ ስቴፈን ሰኩር ለምን የጨፍጫፊውን የደርግ ስርዓት አባል እና ባለስልጣን እንደነበሩ ሲጠይቃቸው የሰጡት መልስ ሁላችንም ያስገረመ መልስ ነበር፡፡ የደርግ አባል የሆኑት እና ከደርግ ጋር ያገለገሉት ጊዚያቶች ልጆቻቸውን ለማሳደግ ሲሉ እንደነበረ በድፍረት ተናግሯል ገልፀዋል፡፡ ለልጆቻቸው ሲሉ ህፃን እና ኣዋቂ ሳይለይ የጨፈጨፈውን የደርግ መንግስት ባለሥልጣን እንደነበሩ ነው ብራሩት፡፡

እንደ ኢንጂኔር ሃይሉ አባባል የአሰቃቂው የደርግ ስርዓት አባል እንዲሆኑ እና አሁንም ከእስራት ወንጀል ይቅርታ ጠይቀው ከእስር እንዲፈቱ ምክንያት የሆኑት ስለ ፖለቲካ ምንም የማያውቁት ህፃናት ናቸው፡፡ ልዩነቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት የቀጠፈው የደርግ ስርዓት አባል የሆኑት ለልጆቻቸው ሲሉ ሲሆን አሁን ከእስር እንዲፈቱ እንደ ምክንያት የተጠቀሙባቸውም ደግሞ የደርግ አባል ሆነው ያሳደግዋቸው እና በውጭ አገር የሚገኙ የራሳቸው ልጆች ሳይሆኑ በእስር አብሮዋቸው ከነበሩት የጓደኞቻቸው ህፃናት ልጆችን ነው፡፡

በፖለቲካ ህይወታቸው በሰርዋቸው ጥፋቶች ህፃናትን እንደ ምክንያት መፈረጃቸው ለረጅም ግዜ የገፉበት ስልት መሆኑ ግልፅ ቢሆንም የህፃናት መብት ተከራካሪዎች ለምን ይህንን እያለሙ.......................ብሎ መቀለድ ይቻላል፡፡ የሚገርመው ደግሞ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ነው ባዩ ፕሮፌሰር ደግሞ የፖለቲካ ጓደኛቸው ናቸው፡፡

ይህ ዓይነት ፖለቲካና የህፃናት ሽቀጥ ስልት በዓይነቱ ለየት ያለ ስልት ቢሆንም የትም ሊያደርሳችው አይችልም፡፡ ከእስር ያስፈታቸው ምክንያት በግልፅ ጥፋታቸው አምነው ይቅርታ መጠየቃቸውንን እና የበደሉትን መንግስትና ህዝብ በቀሪው የህይወት

ዘመናቸው ጥሩ አስተዋፅኦ በማድረግ እንደሚክሱ አምነው ቢንቀሳቀሱ ለራሳቸውም ለሌሎች ተቋዋሚ ሃይሎችም ጥሩ ይሆናል፡፡

የፖለቲካ ህይወታቸው ወደ ማይመለከተው አካል ማላከካቸው ግን ተመልሰው ወደ ተመሳሳይ ጥፋት መግባት ነው እና ከእንደዚህ ዓይነቱ የጥፋትና የወንጀለኝነት አዙሪት እንዲላቀቁ ከቅን ልቦና ተነስተው የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ያደረጉላቸውን ይቅርታ አመስግነው በተግባር ማሳየት መቻል አለባቸው እላለሁ፡፡

**ገብረስላሴ ገብረመድህን**

**<u>ከአዲስ አበባ</u>**